# የ ደ ብ ረ ፡ ሊ ባ ኖ ስ ፡ ታ ሪ ክ ።

D.N Solomon Yohannes
0111/271609

ተ ጻ ፈ ፡
## ከፀባቱ ፡ ኃይለ ፡ መስቀል ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖስ ።


ተነትመ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በሯወጄቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

ወበጄቱ ፡ ሢመተ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስናሁ ፡ ለብፁዕ ፡ አባ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳተ ፡ ዘኢትዮጵያ ።

አ. አ. ........................ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡

በተስፋ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

www.ethiopianorthodox.org



አፄ ፡ ምኒልክ፡ ያሳነፁት ፡ የጥንቱ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።



ትልቁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጻድቅ ፡
አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org



አባ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

www.ethiopianorthodox.org

## የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ታሪክ ።

ከአፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ተጻፈ ፡ ከፀባቴ ፡ ኃይለ ፡ መስቀል። ወከነ ፡ በውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ሐድሶ ፡ ሕንጻታ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ እንተ ይእቲ ፡ መካነ ፡ አፅሙ ፡ ለቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በ፲ቱ ወ፱ቱ ፡ ፻ ፡ ፵ ፡ ወ፱ቱ ፡ ዓመት ፡ በ፳ ፡ ወ፮ቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ወበመዋዕሊሁ ፡ ለአብ ፡ ብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አባ ፡ ባስልዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ወእጨጌ ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ እምአመ ፡ ነበረ ፡ በመንበረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በ፳ ፡ ወ፪ ፡ ዓመት ፡ በወርኃ ፡ ጥር በዘመነ ፡ ማቴዎስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ለዘወጠኑ ፡ ዘንተ ፡ ሕንፀተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያፈጽሞሙ በዳኅና ፡ ወበሰላም ፡ አሜን ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ አሜን ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ወጻድቅ ፡ አባ ፡ ተክለ ሃይማኖት ፡ ዘኃቤሁ ፡ ይነብር ፡ ኵሉ ፡ መራሁተ ፡ ቤተ ፡ ዳዊት ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ አልበ ዘያርሁ ፡ ወአልበ ፡ ዘየአፁ ፡ እንበሌሁ ፡ ብለን ፡ ለንግግራችን መነሻ ፡ እናደርጋለን ።

ጌታችን ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባቶቻችን ፡ ሐዋርያትን ፡ ሑሩኬ ፡ ወመሐሩ ፡ ኵሎ ፡ አሕዛበ ፡ ወእንዘ ፡ ታጠምቅዎሙ ፡ በሉ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወመሐርዎሙ ፡ ኵሎ ፡ ይዕቀቡ ፡ ዘአዘዝኩክሙ ፡ ወናሁ ፡ አነ ፡ እሄሉ ፡ ምስሌክሙ ፡ እስከ ፡ ህልቀተ ዓለም ። ሂዳችሁ ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ አስተምሩ ፡ ስታጠም

www.ethiopianorthodox.org

ቋቸውም ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እያ
ላችሁ ፡ አጥምቋቸው ፡ ያዘዝኳችሁን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ አስ
ተምሯቸው ፡ እኔም ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽ
አት ፡ ድረስ ፡ አድሬባችሁ ፡ እኖራለሁ ፡ ማቴ ፡ ምዕ ፡ ፳፰
ቍ ፡ ፲፱ ።

፪ኛም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ ሐር ፡ ከመ ፡ ትጹር ፡ ስምየ
በውስተ ፡ አሕዛብ ፡ እንዳለው ፡ ግብረ ፡ ሐዋ ፡ ምዕ ፡ ፱ ፡ ቍ
፲፫ ፡ አባታችን ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትንም ፡ አ ፍቁርየ
ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አኮኑ ፡ አነ ፡ ፈነውኩከ ፡ ትሥዓር ፡ ጣዖ
ታተ ፡ ወትቀድስ ፡ ታቦተ ፡ ወትሢም ፡ ካህናተ ፡ ወዲያቆናተ
እስመ ፡ አነ ፡ ረሰይኩከ ፡ ብርሃነ ፡ ዓለም ፡ ከማየ ፡ በውስተ
ዛቲ ፡ ብሔረ ፡ ጽልመት ። ወዳጄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሆይ
ቀሳውስት ፡ ዲያቆናትን ፡ በአንብሮተ ፡ ዕድ ፡ ልትሾም ፡ ታቦ
ትን ፡ ቀድሰህ ፡ ልታከብር ፡ ጣዖታትን ፡ ልታጠፋ ፡ ድንቁ
ርና ፡ በፀናባት ፡ በዚች ፡ ሃገር ፡ እንደእኔ ፡ የዓለም ፡ ብርሃን
አድርጌ ፡ ልኬሐለሁ ፡ ብሎ ፡ ስለሾማቸው ፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያ
ስብከተ ፡ ወንጌልን ፡ ዘርግተው ፡ በሰፊው ፡ አስተምረዋል ።

ይልቁንም ፡ በወላሞ ፡ አውራጃ ፡ ሞተለሚ ፡ የተባለ
ውን ፡ ዓላዊ ፡ ንጉሥ ፡ ከነሕዝቡ ፡ መክረው ፡ አስተምረው
ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከገ
ቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ መልሰው ፡ በብዙ
ድካም ፡ የሐዋርያነት ፡ ተግባራቸውን ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡
ሕገ ፡ ምንኩስናን ፡ ለመፈጸም ፡ ይህንን ፡ ገዳም ፡ መሠረቱ ።

ከዚህም ፡ ጥቂት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የ፳ኤል ፡ መንግ
ሥት ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በትውልድ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣ
ው ፡ ከመሠረቱ ፡ ተናውጾ ፡ ወደ ፡ ነገደ ፡ ዛጔ ፡ ሄዶ ፡ ነበርና ፡
የዚህ ፡ መንግሥት ፡ ተወላጅ ፡ የሆኑት ፡ ፳ኤላዊው ፡ አፄ ፡
ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ስለ ፡ መንግሥታቸው ፡ መመለስ ፡ እንዲ



ጸልዩላቸው ፡ አዝነው ፡ ቢለምኗቸው ፡ በዚሁ ፡ በታ ፡ ሳሉ
ስፈጣሪያቸው ፡ አመልክተው ፡ ከመሠረቱ ፡ ተናውጾ ፡ የነበ
ረውን ፡ መንግሥት ፡ መልሰው ፡ ለተወላጁ ፡ ለአፄ ፡ ይኩኖ
አምላክ ፡ ካሰጡ ፡ በኋላ ፡ ሁሉን ፡ ማድረግ ፡ የሚቻለው ፡
እግዚአብሔር ፡ የኔን ፡ ያገልጋዩን ፡ ልመና ፡ ሰምቶ ፡ ያባት
ህን ፡ መንግሥት ፡ መልሶልሐል ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖትን ፡ ሳት
ክድ ፡ አምልኮተ ፡ በዕድ ፡ ሳትወድ ፡ መካነ ፡ አዕሚን ፡ ሳታ
ዋርድ ፡ ለኔ ፡ መታሰቢያና ፡ በመንፈስ ቅዱስ ፡ ከኔ ፡ ለሚ
ገኙ ፡ ልጆቼ ፡ መረጃ ፡ የሚሆን ፡ የመንግሥትህን ፡ ሲሶ ፡ ሰጥ
ተህ ፡ ብትኖር ፡ መንግሥትህን ፡ ለልጅ ፡ ልጆችህ ፡ ታወር
ሳለህ ፡ አሏቸው ።

አፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክም ፡ ይህንን ፡ ቃለ ፡ መሐላ ፡ አላ
ፈርስም ፡ ብለው ፡ ከመንግሥታቸው ፡ ሲሶውን ፡ ለደብረ ፡
ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ ሊሰጡ ፡ ገዳሙንም ፡ በሕገ ፡ መንግሥታ
ቸው ፡ ሊጠብቁ ፡ አምላካዊ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተገባብተው ፡
ይኸው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በወራስያነ ፡ መንግሥታቸውና ፡ በደ
ቂቀ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መካከል ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ሠንሰ
ለት ፡ ሆኖ ፡ የገዳሙን ፡ ክብር ፡ በሕግ ፡ ሲጠብቅ ፡ ይኖራል ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የዚህ ፡ መንግሥት ፡ ወራሾች ፡ የሆ
ኑ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን
ከመጠበቃቸውም ፡ በላይ ፡ በዘመናቸው ፡ ታላላቆች ፡ አብ
ያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እያሠሩ ፡ ለአባታችን ፡ ገዳም ፡ ለደብረ
ሊባኖስ ፡ ሰጥተዋል ፡ ይህንንም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ባለው ፡
መስመር ፡ እንገልጻለን ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሥርዓት ፡ ከአ
ቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ከአፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ጀምሮ
እስከ ፡ እጨጌ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማና ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕ
ቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ ሀብቱም ፡ ትሩፋቱም ፡

www.ethiopianorthodox.org

እየተጨመረና ፡ እየተስፋፋ ፡ ይሄድ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ጥንታ
ዊው ፡ ታሪክ ፡ አስረድቶናል ።

በአፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብና ፡ በእጨጌ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡ ግን
ሥርዓቱም፡እያማረ ፡ ትሩፋቱም፡ እየበዛ ፡ በመሔዱ ፡ በየአድ
ባራቱ ፡ ሁሉ ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሥርዓት ፡ ይሁን ፡ ተብሎ
እንደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተሠርቷል ።

አፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ መቶ
ሃምሳ ፡ ቀላድ ፡ ሰጡ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖችም ፡ ፩ኛ ፡ ደብረ፡ብ
ርሃን ፡ ፪ኛ ፡ ደብረ ፡ ምጥማቅ፡ ፫ኛ ፡ ደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ የሚ
ባሉትን ፡ ሠርተው ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሰጡ ።

እንዲሁም፡ ከደብረ፡ ሊባኖስ፡ ሁለት፡ መነኮሳት ፡ አስመጥ
ተው፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አስቀምጠው ፡ ስለሃይማኖትና ፡
ስለሕግ ፡ መንግሥቱ ፡ እየመከሩ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ ጉዳ
ይ ፡ እያስታወሱ ፡ ይቀመጡ ፡ ብለው ፡ ሥርዓት ፡ ሠሩ ፡ ይኸ
ውም ፡ ሥርዓት ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ይሁ
ን ፡ ብለው ፡ ወስነዋል ፡ ለመነኮሳቱም ፡ ድርጎ ፡ በየዕለቱ፡ሳ
ይጓደል ፡ በ፲፰ ፡ ሰው ፡ ልክ ፡ ይሠጣቸው ፡ ብለው ፡ ከቢት
ወደዱ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጭንጫ ፡ አሽከሩ ፡ ታዞ ፡ እንዲሰጥ
በአቡነ ፡ መርሐ ፡ ክርስቶስ ፡ ጊዜ ፡ ተሠርቷል ።

አፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምም ፡ አትሮኑሰ ፡ ማርያም ፡ ደብረ
ማርያም ፡ የሚባሉ፡ ሁለት፡ ቤተ፡ መቅደሶች ፡ ሠርተው ፡ ለደ
ብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሰጡ ።

እጨጌውንም ፡ አቡነ ፡ መርሐ ፡ ክርስቶስን ፡ በክብር
ላይ ፡ ክብር ፡ ጨመሩላቸው ፡ ንጉሥ ፡ እስክንድርም ፡ ደብረ
ምስጢርና ፡ ገነተ ፡ ጊዮርጊስ፡የሚባሉትን ፡ ቤተ ፡ መቅደሶች
ሠርተው ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሰጡ ።

እጨጌውንም ፡ በክብር ፡ ከማኅበሩ ፡ ጋር ፡ ተቀምጠው
የንጉሥን ፡ ቃል ፡ ይስሙ ፡ ብለው ፡ ወሰኑ ። እናታቸውም



ንግሥት ፡ ሮምና ፡ ምዕራፈ ፡ ማርያምን ፡ አሠርተው ፡ ለደብ
ረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሰጡ ። አፄ ፡ ናዖድም ፡ በእጨጌ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘ
መን ፡ መካነ ፡ ሥላሴን ፡ ሠርተው ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሰጡ ።

ለእጨጌውም ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ፪ ፡ ድባብ ፡ ይያዝላቸው
ብለው ፡ አዘዙ ፡ ይኸውም ፡ በየጊዜው ፡ ለሚሾሙት ፡ እጨጌ
ዎች ፡ ሁሉ ፡ ሥርዓት ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ ወስነዋል ፡ ቀጥሎ
ም ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ አንጾኪያ ፡ የምትባለውን
ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አሠርተው ፡ ለዚሁ ፡ ገዳም ፡ ሰጥተዋል ።

የአፄ ፡ ናዖድ ፡ እናት ፡ ንግሥት ፡ ሞገሳም ፡ ጌቴሴማኒ
የምትባለውን ፡ አሠርተው ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሰጡ ፡ ይህ
ሁሉ ፡ የነገሥታቱ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ የተፈጸመው ፡ ከግ
ራኝ ፡ በፊት ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ በሰማ
ዕቱ ፡ በእጨጌ ፡ ዮሐንስ ፡ ጊዜ ፡ ግራኝን ፡ ገድለው ፡ ኢትዮጵ
ያን ፡ ከያዙ ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ ገዳም ፡ የፈረሰውን ፡ ቤተ ፡ ክ
ርስቲያን ፡ አሠርተው ፡ ታቦቱን ፡ አነግሣለሁ ፡ ብለው ፡ ቢመ
ጡ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ ያማረ ፡ ሥርአቷን ፡ አይተው ፡ እ
ጅግ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ብዙ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖና ፡ ልዩ፡ልዩ፡
የሆነ ፡ ሸልማት ፡ ሠጥተው ፡ ከመቅደሱ ፡ ጀምረው ፡ እስከ
ውጭው ፡ እድሞ ፡ ድረስ ፡ ምንጣፍ ፡ አስነጥፈው ፡ እንደመ
ለከት ፡ የሚነፋ ፡ ጽበ ፡ አንበሳ ፡ እንደነጋሪት ፡ የሚመታ
ምክረ ፡ ቃና ፡ የሚባል ፡ በአባታችን ፡ በአቡነ፡ ተክለ ፡ ሃይ
ማኖት ፡ በትልልቆቹ ፡ በዓላት ፡ እንዲመታ ፡ አዘዙ ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ ለገዳሙ ፡ መርጃ ፡ እዲሆን ፡ ፩ ፡ ሺ
ቀላድና ፡ ተድባበ ፡ ማርያም ፡ የምትባለውን ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ አሠርተው ፡ ሰጡ ።

አፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግልም ፡ ድበ ፡ አንበሳና ፡ የወርቅ
ወንጌል ፡ ሰጥተው ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ የመጣ ፡ መልክተኛ
ሳይከለከል ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ገብቶ ፡ በገዳሙ ፡ ላይ ፡ የደ

www.ethiopianorthodox.org

ረሰውን ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ ያመልክት ፡ ብለው ፡ የወሰኑት ፡ ውሳኔ ፡ ከአፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ እስከ ፡ ሥግው ፡ ቃል ፡ ከሥግው ፡ ቃል ፡ እስከ ፡ ኒጋሜ ፡ ክርስቶስ ፡ ከኒጋሜ ፡ ክርስቶስ ፡ እስከ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ከሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ደንብ ፡ ጸንቶ ፡ ቆይቷል ።

የአፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ እናት ፡ ንግሥት ፡ አድማስ ሞገሳ ፡ የሚባሉ ፡ ማሕፊደ ፡ ማርያም ፡ የምትባል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠርተው ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሰጥተዋል ። ንጉሥ ፡ ወሰን ፡ ሰገድም ፡ ከ፫ ፡ መቶ ፡ የሚበልጥ ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳትና ፡ መጻሕፍት ፡ ሰጥተዋል ።ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴም ፡ ፩ኛ ወይበ ፡ ከሚባለው ፡ ቀበሌ ፡ ፱ ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ ፪ኛ ፡ በተጉለትና ፡ በቡልጋ ፡ አውራጃ ፡ ውስጥ ፡ ካሰት ፡ የተባለውን ፫ኛ ፡ አጋዘን ፡ በር ፡ በጠቅላላው ፡ ፲፪ ፡ ጋሻ ፡ የሚሆን ፡ ርስት ፡ ሰጥተዋል ፡ ቀጥሎም ፡ በዚሁ ፡ ገዳም ፡ አቅራቢያ ፡ ወከና ፡ አራሾ ፡ አንቂ ፡ እነጐታም ፡ የሚባሉትን ፡ ቀበሌዎች ፡ ግብሩ ፡ ከገዳሙ እንዳይወጣ ፡ በውግዘት ፡ አጽንተው ፡ ሰጥተዋል ።

አፄ ፡ ዮሐንስም ፡ በዚሁ ፡ በአባታችን ፡ አፅም ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ የአማረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠርተው ፡ ብዙ ፡ ዘመን ሲሠለስበትና ፡ ሲቀደስበት ፡ ኖሯል ።ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በጐንደር መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ በስደት ፡ እፀጌ ፡ ዘትረ ፡ ወንጌልና ፡ ማኅበሩ ፡ ታቦተ ፡ ማርያምን ፡ ይዘው ፡ ተሰደው ፡ መንግሥቱ ወደሸዋ ፡ ሲመለስ ፡ ታቦተ ፡ ማርያም ፡ ቀርታ ፡ ስለነበር ፡ ከጐንደር ታቦተ ፡ ማርያምን ፡ አስመጥተው ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ በገባች ጊዜ ፡ ለአስተርእዮ ፡ ማርያምና ፡ ለአባታችን ፡ ለ፪ቱ ፡ በዓላት ዝክር ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ አሊዶሮ ፡ የተባለውን ፡ ቀበሌ ፡ ቆላውንም ፡ ደጋውንም ፡ ግብዝናውን ፡ ለራስ ፡ ዳርጌ ፡ ሰጥተው



ዝክሩ ፡ እንዳይታጐል ፡ በውግዘት ፡ አጽንተው ፡ ፫ ፡ ጋሻ ፡ መሬት ሰጥተዋል ፡ ከዚህም ፡ ቀጥለው ፡ በዚሁ ፡ በአባታችን ፡ አፅም ፡ ላይ አሁን ፡ ያለውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲመሠርቱ ፡ ጉረኔና ፡ ዋዩ ከሚባሉ ፡ ቀበሌዎች ፡ የ፲፪ ፡ ሰንጋ ፡ መሬት ፡ ጉልት ፡ በዚሁ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ፫፮ ፡ ጋሻ ፡ የማደሪያና ፡ የገባር ፡ መሬት ግብሩን ፡ ከነዳኝነቱ ፡ በጠቅላላ ፡ ወረዳውን ፡ ለገዳሙ ፡ መርጃ ይሁን ፡ ብለው ፡ ሰጥተዋል ።

ቀጥሎም ፡ በወላሞ ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ዳሞት ፡ የተባለውን ፡ ጻድቁ ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ ያደረጉበት መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ በአባታችን ፡ በአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠርተው ፡ ልዩ ፡ ስሙን ፡ ደብረ ፡ መንክራት ፡ ብለው ፡ ሰይመው ፡ ለገዳሙ ፡ መተዳደሪያ ፡ ብዙ ፡ የገባር ፡ መሬትና ፡ በጠቅላላ ፡ የአውራጃ ፡ ሊቀ ካህናትነቱን ፡ ለዚሁ ፡ ገዳም ፡ ሰጥተዋል ።

ልዑል ፡ እራስ ፡ መኰንንም ፡ ለአባታችን ፡ ቤት ፡ ለደካማ ፡ መርጃ ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ ሆሴ ፡ ከሚባለው ፡ ቦታ ፡ ፲፩ ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ ሰጥተዋል ። እንዲሁም ፡ ግርማዊነታቸው ፡ አሁን ፡ የአባታችን ፡ መስቀልና ፡ ታቦተ ፡ ማርያም ፡ ያሉበትን ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አሠርተው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲነገርበት ፡ ይኖራል ።ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በዚሁ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ለሚያገለግሉ ፡ ካህናት ፡ በአሩሲ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ፶ ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ ሰጥተዋል ።

ከዚህም ፡ የበለጠ ፡ ሐሳባቸው ፡ አልቦ ፡ እምቅድሜከ ወአልቦ ፡ እምድኅሬከ ፡ ተብሎ ፡ በፈጣሪው ፡ ቃል ፡ የተመሰገነ ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ ሀገሩ ፡ ለንጉሥ ፡ ዓቢይ ፡ በተባለችው በቅድስት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አሠርቶ ፡ የፈጣሪውን ፡ ስም ፡ ሲያስመሰግን ፡ እንደኖረ ፡ በበጎ ምግባርና ፡ በአርቶዶክስ ፡ ሃይማኖት ፡ ፍጹም ፡ የሆኑ ፡ ግር

www.ethiopianorthodox.org

ማዊነታቸውም ፡ በፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸንተው ፡ በአባታቸው ፡ በቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አፅም ፡ ላይ ፡ ለስሙ መመስገኛ ፡ የሚሆን ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ሊሥሩ ፡ በፍጹም ልቦናቸው ፡ መዘጋጀታቸው ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ነቢዩ ፡ ዘካርያስ ፡ የዘሩባቤል ፡ እጆች ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ መሠረቱት ፡ እጆቹም ፡ ይፈጽሙታል ፡ ብሎ ፡ እንዳጽናናውና ፡ እንዳበረታታው ፡ አምላክ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ግርማዊነታቸውንም ፡ በእድሜና ፡ በደስታ ፡ አድሶ ፡ አበርትቶ ፡ የአባታችን ፡ የቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ቤተ መቅደስ፡የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ፡አፄ ፡ ኃይለ፡ሥላሴ ፡ እጆች ፡ መሠረቱት ፡ እጆቻቸውም ፡ ፈጸሙት ፡ ለመባል ፡ ያበቃን ፡ ዘንድ ፡ በፍጹም ፡ ልቦናችን ፡ እንመኛለን ፡ አሜን ።

ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ አባታችን ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለስብከተ ፡ ወንጌል ፡ ያሰማሯቸውን፡ ንቡራነ ፡ ዕድና ፡ ቆሞሳት፡ የሆኑትን ፡ መነኰሳት ፡ ዝክረ ፡ ስማቸውን ፡ ሀገረ ፡ ስብከታቸውን ፡ ገልጸነዋል ፤ አባ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቆሞስ ፡ በእቢበሎ፡ ትግሬ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ፡ በሰልዋ ፡ ትግሬ ፡ አባ ፡ መድኃኒነ ፡ እግዚእ ፡ በደብረ ፡ ኃይል ፡ ትግሬ ፡ አባ ፡ አግናጥዮስ ፡ በጉንዳጉዲ ፡ ትግሬ ፡ አባ ፡ ዳንኤል ፡ በዓቢየ ፡ እግዚእ ፡ ትግሬ ፡ አባ ፡ በርተሎሜዎስ ፡ በደብረ ፡ አፍላ ፡ ትግሬ ፡ አባ ፡ ክርስቶስ ፡ ሞዓ ፡ በደርጋ ፡ ትግሬ ፡ ፱ኛ ፡ አባ ፡ በርተሎሜዎስ ፡ በጀን ፡ አሞራ ፡ በጌምድር ፡ አባ ፡ ዮሴፍ ፡ በመቅደላ ፡ አንገት ፡ በጌምድር ፡ አባ ፡ አሮን ፡ በላይ፡ በጌምድር ፡ አባ ፡ ብንያም ፡ በታች ፡ በጌምድር ፡ አባ ፡ ሰላማ፡ በሙጃ ፡ በጌምድር ፡ አባ ፡ ማትያስ ፡ በእንፍራንዝ ፡ በጌምድር ፡ አባ ፡ አርአየነ ፡ ጸጋሁ ፡ በደደክ ፡ በለሳ ፡ በጌምድር ፡ አባ፡ዮሐንስ ፡ በወፍ ፡ አንቂ ፡ በጌምድር ፡ አባ ፡ እንድርያስ፡ በቆለላ ፡ ጎጃም ፡ አባ ፡ ዮሴፍ ፡ ዳሞት ፡ ጎጃም ።



በሸዋ ፡ አውራጃ ፡ አባ ፡ ይትባረክና ፡ አባ ፡ ማርቆስ ፡ በደማስቆ ፡ አባ ፡ ተስፋ ፡ ሥላሴ ፡ በታች ፡ ወለቃ ፡ ዶራ ፡ ቦረና ፡ መርሐ ፡ ቤቴ ፡ አባ ፡ ክርስቶስ ፡ ቤዛነ ፡ በአመልሳ ፡ መርሐ ፡ ቤቴ ፡ አባ ፡ ፊንሐስ ፡ በአባሰል ፡ በየጁ ፡ አባ ፡ ሉቃስ ፡ በሐይቅ ፡ አባ ፡ ሚናስ ፡ በቀወት ፡ አዳል ፡ እስከ ፡ ጥልጣል ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ናዝራዊ ፡ በጓይ ፡ አንገቻ ፡ መንዝ ፡ አባ ፡ ፊቅጦር ፡ በየሻ ፡ ይፋት ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ በአጎራ ፡ በደንስ ፡ ይፋት ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ በመንግሥት፡ ይፋት፡ አባ ፡ ሕፃን ፡ ሞዓ ፡ በደብረ ፡ በግዕ ፡ ጠራ ፡ እጨጌ ፡ ዮሐንስ፡ በሳፍጅ ፡ ጠራ ፡ አባ ፡ አኖሬዎስ ፡ በሞረት ፡ በወግዳ ፡ በተጉለት ፡ አባ ፡ እንድርያስ ፡ በገሮማ ፡ እንሳሮ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ፡ በክልዓት ፡ አባ ፡ መስቀል ፡ ሞዓ ፡ በሙገር ፡ ሰላሌ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ በወይበ ፡ ፍቼ ፡ ሰላሌ ፡ አባ ፡ ፊላታዎስ ፡ በምድረ ፡ ክብድ ፡ በጉራጌ ፡ በምሁር ፡ አባ ፡ አርከ ፡ ሕፃን ፡ በቡልጋ፡ አባ ፡ አኖሬዎስ ፡ በባሌ ፡ በሐረር ፡ አባ ፡ ኃብተ ፡ ማርያም ፡ በዚይ ፡ በአሩሲ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ በአምባርኢ ፡ ከንባታ ፡ አባ ፡ እንድርያስ ፡ በዳሞት ፡ ወላሞ ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ዋኅድ ፡ በሲዳሞ ፡ በቦረና ፡ አባ ፡ ናትናኤል ፡ በገሙ ፡ ብርብር ፡ አባ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐረዮ ፡ በቍጫ ፡ በጎፋ ፡ በባኮ ፡ አባ ፡ ተስፋ ፡ ሕፃን ፡ በሃገሩ ፡ በደወሮ ፡ በጅማ ፡ በዛንጀሮ ፡ አባ ፡ አብርሃም፡ በኩፋ ፡ በማጅ ፡ በይሉባቦር ፡ አባ ፡ ማትያስ ፡ በወለጋ ፡ እስከ፡ ሻንቅላ ፡ ተሾመው ፡ ሄዱ

አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በተወለዱ ፡ በ፺፰ ፡ ዓመት ፡ በ፯ሺ ፡ ፮፻፶፮ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ በ፩ ፡ ቀን ፡ ፵፯ ፡ መምህራን ፡ በየሀገሩ ፡ ሾመዋል ፤ ፲፪ ፡ ንቡራነ ፡ ዕድ ፡ አባ ፡ አኖሬዎስ ፡ ዘጽጋጃ ፡ አባ ፡ ታዴዎስ ፡ ዘጽላልሽ ፡ አባ ፡ ገብረ፡ ክርስቶስ ፡ ዘድቢ ፡ አባ ፡ ዮሴፍ ፡ ዘናርዕት ፡ አባ ፡ አድኃኒ፡ ዘዳሞት ፡ አባ ፡ ኢዮስያስ ፡ ዘወጅ ፡ አባ ፡ ማትያን ፡ ዘፊጠ

www.ethiopianorthodox.org

ጋር ፡ አባ ፡ ቀውስጦስ ፡ ዘመሐግል ፡ አባ ፡ አኖሬዎስ ፡ ዘወግዳ ፡ አባ ፡ መርቆሬዎስ ፡ ዘመርሐ ፡ ቤቴ ፡ አባ ፡ ዜና ፡ ማርቆስ ፡ ዘሞረት ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ዘወገግ ፡ እነዚህ ፡ ፲፪ ፡ ንቡራን ፡ ዕድ ፡ እንደ ፡ ፲፪ ፡ ሐዋርያት ፡ የቀሩት ፡ እንደ ፡ ፸፪ ፡ አርድእት ፡ ሆነው ፡ አባታችን ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ መስለው ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሙሉ ፡ ከላይ ፡ በስም ፡ ለተጠቀሱት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቶቻቸው ፡ በዕፃ ፡ አካፍለው ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ እያሣነጹ ፡ ሕዝቡን ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ከሕገ ፡ ኦሪት ፡ ወደ ፡ ሕገ ፡ ወንጌል ፡ መልሰው ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ብሂል ፡ ተክለ ፡ አብ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ ተክለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ ብርሃነ ፡ ዓለም ፡ ተብለዋል ።

ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በዚሁ ፡ ገዳም ፡ ላይ ፡ የተባሕትዎን ፡ ተግባር ፡ በመፈጸም ፡ ለፈጣሪያቸው ፡ ያደረጉት ፡ አገልግሎት ፡ እራሳቸውን ፡ ጠቅሞ ፡ ለሙሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ አማላጅነታቸው ፡ የታወቀ ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዳን ፡ አልበሙ ፡ ድሂን ፡ ለሰብአ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘእንበለ ፡ ረድኤተ ፡ ጸሎቱ ፡ ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚል ፡ ማስረጃ ፡ በገድላቸው ፡ ተጽፎ ፡ እናገኛለን ፡ ይህንኑ ፡ ቃል ፡ ኪዳናቸውን ፡ ምክንያተ ፡ ድኅነት ፡ በማድረግ ፡ ከዓፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ገሮምሮ ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ በጻድቁ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አዝማነ ፡ መንግሥታቸው ፡ እንዲረዝምላቸው ፡ ጠላቶቻቸው ፡ እንዲደክሙላቸው ፡ በማሰብ ፡ ይልቁንም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ በዓፀደ ፡ ሥጋ ፡ መለየት ፡ የማይቀር ፡ ስለሆነ ፡ ተስፋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በማሰብ ፡ ለስማቸው ፡ መጠሪያ ፡ እንዲሆናቸው ፡ በዚሁ ፡ ገዳም ፡ ላይ



አንዳንድ ፡ መታሰቢያ ፡ ሳያቆሙ ፡ ያለፉ ፡ ነገሥታት ፡ የሉም በታይቱም ፡ በቃል ፡ ኪዳናቸው ፡ ከብሩ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማደሪያ ፡ ስለሆነች ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሀገሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወማኅደረ ፡ ፍሥሐሆሙ ፡ ለነገሥተ ፡ ኢትዮጵያ ።

ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይትመሐፀኑ ፡ ወእለ ፡ ያስምኩ ፡ ባቲ ፡ ተብሎ ፡ ቃል ፡ ኪዳናቸውን ፡ በመተማመን ፡ ለተማጸኑባት ሁሉ ፡ ትንቢት ፡ ተነግሮላቸዋል ፡ ጥፋቷን ፡ ለሚያስቡና ፡ የጻድቁን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በማቃለል ፡ ክፉ ፡ አድራጎት ፡ የሚመኙባትን ፡ ግን ፡ ወአድክም ፡ መጻርርቲሃ ፡ ወእሞቅሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይገብሩ ፡ ሀከከ ፡ በውስቴታ ፡ ተብሎ ፡ ትንቢት ፡ ተነግሮባቸዋል ፡ ስለዚህ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለሮም ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ ፲ ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፭ ፡ ቍጥር ፡ ነአምርከመ ፡ ይረድኦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእለ ፡ ያፈቅርዎ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ፡ በበገ ፡ ምግባር ፡ ጸንተው ፡ በገ፡ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የሚያገለግሉትን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲረዳቸው ፡ እናውቃለን ፡ ያለውን ፡ ትንቢታዊ ፡ ነገር ፡ ስንመለከተው ፡ አሁን ፡ የተመሠረተው ፡ ሕንፃ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን « ወትትሐነጽ ፡ በስምከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠናይት ወይሄሉ ፡ ውስቴታ ፡ ጸጋየ ፡ ወሰላምየ ፡ እስከ ፡ ኅልቀተ ፡ ዓለም ፡ የሚል » በጻድቁ ፡ በቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ገድል ፡ ተጽፎ ፡ ያገኘነው ፡ የትንቢቱ ፡ ሁሉ ፡ መፈጸሚያ ፡ አሁን ፡ በንጉሡ ፡ ነገሥታችን ፡ በአፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ መሆኑን ፡ ስለተረዳነው ፡ እኛም ፡ ይህንኑ ፡ ትንቢት ፡ በመረዳት ፡ ንሕነኒ ፡ ንበል ፡ አሜን ፡ ሃሌ ፡ ሉያ እጹመ ፡ ዘንተ ፡ ብእሴ ፡ መተንበለ ፡ ወዘንተ ፡ ቅዱሰ ፡ መንሥኤ ፡ ወዘንተ ፡ መምህረ ፡ መምህፃን ፡ ዘወሀበነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴሃ ፡ ነቢየ ፡ በከመ ፡ ወሀበሙ ፡ ለጀኤል ፡

www.ethiopianorthodox.org

መምህፃነ ፡ ሙሴሃ ፡ ነቢየ ፡ ወይእዜኒ ፡ ወሀበነ ፡ ዘንተ ፡ አበ
መሥተስርየ ፡ አበሳነ ፡ በስእለቱ ፡ ወመንጽሄ ፡ ኃጢአትነ ፡ በ
ጸሎቱ ፡ ወወሀበነ ፡ ዛተ ፡ ምድረ ፡ መካነ ፡ መቃብሪሁ ፡ ለዝ
ንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከመ ፡ ኃዊረነ ፡ ሃቤሀ
ንድኃን ፡ እምቀትለ ፡ ሞት ፡ ወሲኦል ፡ ዘያኃጉል ፡ ነፍሰ ፡ ለ
ዓለመ ፡ ዓለም ።

ጸሎቱ ፡ ወስእለቱ ፡ ለትሩፈ ፡ ምግባር ፡ ወሃይማኖት ፡
አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይእቀበሙ ፡ ለሊቀ ፡ ጳ
ጳሳት ፡ አባ ፡ ባስልዮስ ፡ ወለንጉሠ ፡ ነገሥትነ ፡ ኃይለ ፡ ሥላ
ሴ ፡ ወለመፃምርቱ ፡ ወለተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወለወራሴ ፡ መንግ
ሥቱ ፡ አምኃ ፡ ሥላሴ ፡ ወምስሌነሂ ፡ ደቂቀ ፡ ክቡር ፡ ተክለ
ሃይማኖት ፡ አሜን ፡ ወአሜን ፡ ለይኩን ፡ ለይኩን ፡፡

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911880113
0111271609
D.N Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org